አለቃቅሳለሁ አላለቅስ እንጂ
የረሃቤ መድሃኒት
እናት አለም ሞታ

# ተናገር



ቅጽ 1 ቁጥር 12

ረቡዕ ሰኔ 1 ቀን 1986 ዓ/ም ዋጋው 0.75 ለአዲስ አበባ

# የሕወሓት መሪዎች ገና ወደፊት ዝርዝሩ ሲወጣ የሚያፍሩበት ታሪክ እንዳላቸው ተገለፀ

ዶ/ር ነገደ ጐበዜ የሕወሓት መሪዎች ገና ወደፊት ዝርዝሩ ሲገለጽ የሚያፍሩበት ታሪክ ያላቸው መሆኑን ገለፁ። ዶክተሩ ይህን የገለፁለት «የጦቢያ» መጽሔት በቅጽ 2 ቁጥር 12 እትሙ የሽግግሩ መንግስት የቀይ ሽብር ወንጀለኛ ነዎት ይላል። ይቀበሉታል? ሲል ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ነው።

ዶ/ር ነገደ ባለፉት 20 ዓመታት አያሌ ሕይወት መጥፋቱን አውስተው «አንዲት እናት ልጇ በመኢሶን ስር ተሰልፎ ተሰዋ ግሩም ነው፤ በኢሕአፓ ባንዲራ ሥር ተሰዋ ጀግናው፣ ለአልባኒያ ኮምዩኒዝም ዓይነት ተዋደቀልኝ ቆራጥ አብዮታዊ ነው፤ በደርግ ባንዲራ ሥር ሞተ ይበለው ከሃዲ ነው አትልም። ያለፉትንም የቀሩትንም ማክበር ማለት ሁሉንም በአንድ ዓይነት ማየት ማለት ነው። ቀጥሎ ይህ ሁሉ ዜጋ መሰዋቱ አስፈላጊ ነበር ወይ? ብሎ መጠየቅ ይገባል። ይህ ሰማዕትነት ደግሞ የትም ባክኖ እንዳይቀር ትምህርት መቅሰም ያስፈልጋል» ካሉ በኋላ፣ በኢትዮጵያ ካሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ እንደዚህ ዓይነቱን የራስ ምርመራ ሂደት መጀመርና ማካሄድ ያለበት አንድ



ዶ/ር ነገደ ጐበዜ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

**«52 በመቶ ቀረጥ የምንከፍል ዜጎች በኤርትራውያን ነጋዴዎች ልንከስም ነው» የጫማ አምራቾች እሮሮ**

ምንም እንኳን ጊዜያዊ የሆነው ፖለቲካ ቢለያየንም በኢኮኖሚ ግንኙነቱና ትስስሩ መሠረት በንግዱ ተግባር ላይ እኩል የሚያድግ ሂደት ካለመፈጠሩ የተነሳ ኤርትራውያን ነጋዴዎች ያለምንም ቀረጥ ጫማ ምርት ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገቡ በመደረጉ እኛ ዜጎች ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሳንከስም አንቀርም ሲሉ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የጫማ ማምረቻ ድርጅት ባለቤት አስታወቁ።

እኛ ከውጭ በምናስገባው ሸቀጥ 12 በመቶ ባመረትነው ላይ ደግሞ 40 በመቶ ቀረጥ ስንከፍል ከኤርትራ ተመርቶ ወደ አገራችን የሚገባው ጫማ ቀረጥ አለመቀረጡ የንግድ አቋማችን በእጅጉ ተናግ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## «ከምርጫው በኋላ ፀረ–ሕዝቦች የሕዝቡን ሰላም ለማጨለም ብዙ ጥረት ማድረጋቸው አይቀርም»

«ከአሁኑ ምልክቱ እንደሚታየው ከምርጫው በኋላ ፀረ–ሕዝቦች የሕዝቡን ሠላም ለማጨለም ብዙ ጥረት ማድረጋቸው አይቀርም። ኢህአዴግ ሠላምን ለማስጠበቅ ሲል ፀረ ሕዝቦች በሚመጡበት መንገድ ሁሉ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል። ሕዝቡም ልማቱን ማፋጠን የሚችለው በያለበት አካባቢ ፀረ ሕዝብ ሃይሎች ሲመክት በመሆኑ ባለው አቅም ሁሉ መሟተፍ ይኖርበታል።» ሲሉ ጠ/ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ጥሪ አዘል መልዕክት አስተላለፉ።

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠ/ሚንስቴርና የብሔረ አማራ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ዋና ፀሐፊ አቶ ታምራት ላይኔ ይህን ጥሪያቸውን ያሰሙት ግንቦት 20ን

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

**ሕገ መንግሥታዊ ሸንጎ የማስመረጥ**

## ሂደት እንዲቆም ተጠየቀ

አቶ አበራ የማነአብ ለፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ ግንቦት 7 ቀን 1986 በፃፉት ግልጽ ደብዳቤ ከተቃዋሚ ኃይሎችና ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ብርቱ ተቃውሞ ያተረፈውን ሕገ መንግስታዊ ሸንጐ የማስመረጥ ሂደት እንዲቆም ጠይቀዋል። አቶ አበራ አያይዘው የመንግስት የቅድሚያ ትኩረት የዜጎችን ሕይወት ማትረፍ መሆኑን በማውሳት አስቸኳይ እርዳታ የማስተባበሩና የማድረሱ ተግባር እንደተጠናቀቀ ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎችና የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያሳትፍ ጉባዔ ተጠርቶ፣ የሽግግሩን ሂደትና ውጤት ለመገምገም ከሁሉም ወገኖች ጋር ከወዲሁ ምክክር መጀመር አስፈላጊ እንደሆነ ጠቁመው፣ ሃገሪቱ ያላትን የሰው ኃይልና የገንዘብ አቅም ወገንን በመዳንና በማቋቋም ተግባር ላይ እንድታውል ለማስቻል መንግስትና ተቃዋሚ ኃይሎች በጋራ እንዲሰሩ ፕሬዚዳንት መለስ ጥሪ እንዲያቀርቡ በደብዳቤአቸው ጠይቀዋል።

አቶ አበራ የሕገ–መንግስታዊ ሸንጐ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

**በጎንደር የኢዲህ አባል ተገደሉ**

## በክልል 3 ሰዎች ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ታሠሩ

በክልል 3 በደቡብ ጎንደር ዞን በሚገኘው የፎገራ ወረዳ ርዕሰ ከተማ በሆነችው በወረታ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች ያለፍ/ቤት ትዕዛዝና ያለፖሊስ መጥሪያ «የሕገመ ንግሥቱን ጉባዔ አባላት ምርጫ ታደናቅፋላችሁ» በሚል ሰበብ በታጣቂዎች ሌሊት ከየመኖሪያ ቤታቸው እየታደኑ መታሰራቸውን ከቦታው የደረሰን ዜና ገልጧል:: ዜናው በ26/9/86 ከሌሊቱ 6 ሰዓት ላይ 1ኛ/ ፶ አለቃ ተሾመ ታደለ የተባለውን ታጣቂዎች ቤቱን ከበው ትፈለጋለህ ብለው ከአስከፈቱት በኋላ እርሱንና ባለቤቱን ደብድበው ልብስናእቃዎቹን በመውረስ ፶ አለቃውን ሲያስሩ ባለቤቱ በዘመድ አዝማድ እርዳታ በሕክምና ላይ መገኘቷን አስረድቷል። 2ኛ/ መምህር ፍላቴ በላይ 3ኛ/ ከንዴ ፈንቴ 4ኛ/ ወጣት ልዑል ሰገድ አደራ የተባሉት በተመሳሳይ ሁኔታ ጥፋታቸው ሳይታወቅ ክስ ሳይመሰረትባቸውና ፍ/ቤትም ሳያውቀውና ትዕዛዝ ሳይሰጥ ተደብድበው መታሰራቸውን የደረሰን ዜና ጨምሮ አስታውቋል።

በሌላ በኩል ደግሞ መሠረት ቀለመወርቅና አየነው ዘለቀ የተባሉት ካለፖሊስ መጥሪያና ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ እጃችንን አንሰጥም በማለት ከመኖሪያ ቤታቸው ራሳቸውን የሰወሩ መሆኑ ተገልጿል። ለጊዜው ማንነቱ ያልታወቀ የወረታ ከተማ አካባቢ ገበሬ በዕለቱ ታፍኖ ተወስዶ እስካሁን የደረሰበት አለመታወቁ ተጠቁሟል።ተያይዞ በደረሰን ዜና በጎንደር ከተማ ነዋሪ የሆኑት ሻምበል መሠረት አስታጥቄ የኢዲኅ አባል የሆኑት ማንነታቸው ባልታወቁ ታጣቂዎች ሰሞኑን መገደላቸውን ከወደ ጎንደር የደረሰን ጥቆማ ገልጿል።

**ኢሠፓ በለንደኑ ጉባዔ ቢሳተፍ ኖሮ**

## የሽግግር መንግሥቱ አባል ይሆን እንደነበር ፕ/መለስ ገለፁ

ኢሠፓ በ1983 ዓ/ም ለንደን በተደረገው የተቃዋሚዎችና የወቅቱ መንግሥት ስብሰባ ላይ የኢህአዴግ ጦር አዲስ አበባን እንዲቆጣጠር በአስታራቂዋ (በአደራዳሪዋ–አሜሪካ) ሲወሰን ጉባኤውን ረግጦ ባይወጣ ኖሮ በሚቋቋመው (በተቋቋመው) የሽግግር መንግስት ውስጥ ተሣታፊና ባለወንበር ሊሆን ይችል እንደነበር ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ ገለፁ።

በአሁኑ ጊዜ በአገሪቷ ውስጥ ምንም አይነት የፓለቲካ እንቅስቃሴ እንዳያደረግና በየትኛውም ስብሰባ እንዳይሳተፍ ማዕቀብ የተጣለበት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) እንደ ፕሬዚዳንት መለስ አገላለፅ« በውይይቱ ተሣታፊዎች ቢሆኑ ምናልባት የሽግግሩ መንግሥት ተሣታፊዎች መሆን አለባቸው የሚለው

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## በውሻ ጩኸት ሰው በጥይት ፤ ዘበኛው በግፍ ተገድለው ተገኙ

በናዝሬት ከተማ በቀበሌ 19 ክልል ውስጥ ይዘዋወር የነበረ አንድ ታጋይ ከሚያልፍበት መንገድ አጠገብ በድንገት አንድ ውሻ ቢጮህበት «ምን ዝም ብለህ ቆመህ ታየኛለህ ፤ በማለት አቶ ተሾመ መርሻ የተባሉትን የአንድ ግለሰብ ቤት ዘበኛ ተኩሶ ታፋቸውን አቁስሎ በሁለተኛው እራሳቸውን ለጥቂት ከሳተ በኋላ ማምለጡን እኚሁ ዘበኛ ለፖሊስ ጣቢያ የሰጡትን ቃል መሠረት በማድረግ ከዚያ የተላከልን ዜና አስታወቀ።

ይህ በውሻ ጩኸት በመደንበር የግድያ ሙከራ የተፈጸመው ግንቦት 26 ቀን 1986 ዓ/ም ሲሆን በማግሥቱ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## አሜሪካ በኤርትራ ራዳርልትተክልነው

አሜሪካ መካከለኛውን ምስራቅ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር የሚችልና በተለይም በኢራን እንቅስቃሴ ላይ የሚያተኩር ራዳር በኤርትሪያ ለመትከል ማናቸውንም ቅድመ ሁኔታ የጨረሰች መሆኑ ታውቋል።

ኤርትሪያ ከኢትዮጵያ የተገነጠለችበትን አንደኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የኤርትሪያን እንቅስቃሴ የዘገበው አንድ የአሜሪካ ጋዜጣ በዚሁ

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## በሜጫና ቱለማ ማህበር ስብሰባ መገኘት የመምረጥ መብትን አሳጣ

በክልል 14 በዞን 3 ወረዳ 19 ሃና ማሪያም ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ የተሰማሩት የኢሕአዴግ አባላት ወጣት ታደሰ ነጋሳ የተባለውን የቀበሌውን ነዋሪና እናቱ በሜጫና ቱለማ ማህበር ስብሰባ ላይ ተገኝታችኋል በማለት የመምረጥ መብታቸው የገፈፋቸው መሆኑን ከሥፍራው የተላከው ዜና አስታወቀ።

ሚያዚያ 20 ቀን 1986 ዓ/ም በዚሁ ቀበሌ ገ/ማህበር ህዝብ እንዲሰበሰብ ተደርጐ የምርጫው አስፈጻሚና የቀበሌው ካድሬ አቶ ተሰፋማሪያም የተባሉት ህዝቡ ድምፁን ለኢሕአዴግ እጩ እንዲሰጥ ቅስቀሳ ሲያደረጉ እንደነበር ዜና አመልክቶ፣በዚሁ ቀበሌ ያሉት ሌሎች አቶ ታምሩ ሳህሌ ፤ አቶ ወርቁ ማሞ እና አቶ መንግሥቱ ሹም የተባሉት የኢሕአዴግ አባላት ህዝቡን እያስፈራሩ የኢሕአዴግ እጩ የህገ መንግሥት ጉባኤ አባላት እንዲመርጡ ከመረጡ ደግሞ ማዳበሪያ በነፃ ሊሰጣቸው እንደሚቻል ሲቀሰቅሱ እንደነበር አስታውቋል። ከዚህም በስተቀር በምርጫው ዕለት ገበሬዎች በየምርጫው ጣቢያ እየተገኙ ድምጽ ካልሰጡ የእርሻ መሬታቸውን እንደሚነጠቁ ካድሬዎቹና የቀበሌው ሹሞች በየመንደሩ እየዞሩ ከማስፈራራታቸውም

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

